DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

Office of Family and Public Engagement

# የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን
# በየጊዜ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን በእያንዳንዱ የኮሎምብያ ግዛት ትምህርት ቤት የሚገኙ የተመረጡ እና የተሾሙ አባላት ቡድን ነው። ቡድኑ ወላጆችን ከፍተኛ የሆነ የሚጠበቁ ነገሮችን ለማሳደግ እና ለተማሪዎች ሁሉ ከፍተኛ ውጤት እንዲያስመዘግቡ የሚያደርጉ ነገሮች ላይ ርዕሰ መምህሩን ለመምከር፣ አስተማሪዎችን፣ በቀጥተኛ በትምህርት ላይ የሚይሳተፉ የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች፣ የማኅበረሰቡ አባላት፣ እና በአንዳንድ ሁኔታዎች ተማሪዎች ይይዛል።

ይህ ዶክመንት ስለአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን እንዴት መስራት እንዳለበት ወዲያውኑ አይቶ ለማወቅ ለሚፈልግ ለማንኛውም ሰው መረጃ ይሰጣል። በአንዳንድ አጋጣሚዎች፣ ይህ ዶክመንት በአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን መምሪያ ውስጥ በ SY15---16 ላይ በሙሉ ገጾች ላይ የሚታይ ሲሆን ይህን ቅጥያ/ተያያዥ ኮፒ በማድረግ በእርስዎ የኢንቴርኔት መፈለጊያ ላይ ሊገኝ ይችላል።
http://dcps.dc.gov/page/local-school-advisory-teams-lsat

---

**ጥያቄ 1፡ ብዙውን ጊዜ የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ምርጫዎች እንዴት ይካሄዳሉ?**

**መልስ 1፡** ምርጫ ብዙውን ጊዜ በየዓመቱ በሜይ 1 እና ጁን 30ኛው ላይ ይካሄዳል። አዲሱ የተመረጠው የአከባብ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን በሚቀጥለው የትምህርት ዓመት ውስጥ ያገለግላል። የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን የአሳቢነት ጀማሪ እና ቀጣይ ድርሻ አካል መሆኑ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ፣ የአከባቢ የትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ለተጨማሪ ዓመት ያገለግላል። ይህ በተለየ ሁኔታ የሚታየው፣ ከላይ ከተሰጠው ምክንያት ጋር፣ ተቀባይነት ለማግኘት ለቤተሰብ እና ለሕዝብ ተሳትፎ ቢሮ መስጠት አለበት (ገጽ 10ን ይመልከቱ)።

---

**ጥያቄ 2፡ በትምህርት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ምርጫዎችን ያላካሄድን ከሆነስ? መቼ ምርጫዎን ሊናካሄድ እንችላለን።**

**መልስ 2፡** አዲሱ የአከባቢ የትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ለቀጣዩ የትምህርት ዓመት ማቀድ እንዲችል ለማድረግ ምርጫዎቹን በሜይ 1ኛ እና በጁን 30ኛ መካከል መደረግ እንዳለበት ሁሉም ጥረቶች ተደርገዋል። ሆኖም ግን፣ ይህ እንዳሆን የሚያደርጉ እንዝላልነት የሚታይባቸው ሁኔታዎች የሚኖሩ ከሆነ፣ ትምህርት ቤቶች አዲሱ የትምህርት ዓመት ከጀመረ በኋላ ወዲያውኑ ቢያንስ ለትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ የሦስት ሳምንት ማስታወቂያ በመንገር ምርጫዎችን ማካሄድ አለባቸው (ገጽ 10ን ይመልከቱ)።

---

**ጥያቄ 3፡ ለወላጆች፣ ለአስተማሪዎች፣ ለሠራተኞች እና ለማኅበረሰቡ አባላት ምርጫዎች በተወሰነ ሥርዓት መካሄድ አለባቸው?**

**መልስ 3:** የወላጅ፣ የአስተማሪ፣ እና በትምህርት ላይ በቀጥታ የማይሳተፉ የሠራተኞች ምርጫዎች በማንኛውም መንገድ ሊደረግ ይችላል፤ ነገር ግን የማኅበረሰቡ አባል በአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ውስጥ እንደሚያገለግል እና እንደማያገለግል ውሳኔ ላይ ከመደረሱ *በፊት* ሁሉም መሚላት አለበት። የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን የማኅበረሰቡን አ ባል በቡድኑ ውስጥ እንዲኖረው ከወሰነ፣ የማኅበረሰቡ አባል ከትምህርት ቤቱ አዋሳኝ አከባቢ የሚኖር መሆ ን አለበት (ገጽ 6ን ይመልከቱ)።

**ጥያቄ 4፡ የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ሊቀመንበር ወይን ጸሓፊ ማን ሊሆን ይችላል።**

**መልስ 4**፡ የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ሊቀመንበር የአሁኑ ተማሪ ወላጅ፣ የአሁኑ አስተማሪ ወይም በአሁን ጊዜ ያለ በትምህርት ላይ በቀጥታ የማይሳተፍ ሠራተኛ አባል *መሆን አለበት* ። ደግሞም ተባባሪ-- ሊቀመናብርት፣ በተለይም ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ወላጅ የሆነ እና በአሁኑ ጊዜ አስተማሪ የሆነ ሊሆን ይችላል። በአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ላይ የማኅበረሰቡ አባል ተወካይ እንደ የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ሊቀመንበር ወይም ተባባሪ ሊቀመንበር ሆኖ ሊያገለግል *አይችልም*። ጸሓፊ የትኛውም የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን አባል ሊሆን ይችላል (ገጽ 8ን ይመልከቱ)።

---

**ጥያቄ 5፡ ወላጆች እንዴት የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ሆነው ይመረጣሉ?**

**መልስ 5**፡ የትምህርት ቤቱ የወላጅ-አስተማሪ ማኅበር፣ የወላጅ አስተማሪ ድርጅት፣ የቤት ለቤት ትምህርት ቤት ማኅበር ወይም በትምህርት ቤቱ ውስጥ ሌላ መደበኛ የሆነ የወላጅ ድርጅት ምርጫውን ሊያሄድ ይችላል። እባክዎትን ያስቡ፡ ወላጅ/ሕጋዊ የሆነ እንክብካቤ ሰጪ አካል ሥራውን ለማካሄድ ወይም የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ሆኖ ለመመረጥ የግድ የወላጅ ድርጅት አካል መሆን የለበትም።

---

**ጥያቄ 6፡ የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን የተለያዩ ዝርያዎች፣ ጎሳዎች፣ ቋንቋ፣ እና የትምህርት ቤቱን ሕዝብ የክፍል ማረጋገጫ ተወካይ አይደለም። በአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድንን የሚወክሉትን ተወካዮች ለማልማት ምን ማድረግ እንችላለን?**

**መልስ 6፡** የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን በሙሉ ከተስማማ፣ የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን የትምህርት ውጤታማነትን እና የብዙኃን ማኅበራዊ ሕይወትን ለማረጋገጥ ብዙ አባላትን ለማካተት ሊስፋፉ ይችላል። የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን አባላት የሚፈቀደው ትልቁ ቁጥር 15 ነው (ገጽ 6ን ይመልከቱ)።

---

**ጥያቄ 7 የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ምን ያህል ጊዜ መሰባሰብ አለባቸው?**

**ጥያቄ 7፡** ቢያንስ የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ቢያንስ በዓመት ውስጥ 4 ጊዜ፣ ሴፕቴምበር፣ ዲሴምበር፣ ፌብሩዋሪ እና ሜይ ላይ መሰብሰብ እንዳለባቸው ይመረጣል። ሆኖም ግን፣ የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ሊሰበሰቡ የሚችሉበት የጊዜ መጠን ምንም ውስንነት የለውም። ቀነ ቀጠሮው ለወላጆች፣ ለትምህርት ቤት ሠራተኞች እና ለርዕሰ መምህሩ የሚመቹ የተለያዩ ቀነ ቀጠሮዎች መያዝ እንዳለባቸው ማሰብ አለባችሁ።

---

**ጥያቄ 8፡ ሁሉም የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ስብሰባዎች ለትምህርት ቤት ማኅበረሰብ ክፍት ናቸው?**

**ጥያቄ 8፡** ሁሉም የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ስብሰባዎች በተለየ ምክንያት ካልተገለጸ በስተቀር ለህትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ ክፍት ይሆናሉ። የስብሰባ ማስታወቂያ በትምህርት ቤቱ ጋዜታ፣ በራሪ ወረቀቶችን ከተማሪ ጋር ወደ ቤት በመላክ እና ወላጆች እና ሠራተኞች ሊያዩት በሚችሉት ቦታ ላይ በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በቋሚነት በመለጠፍ ለቤተሰቦች፣፥ ለሠራተኞች እንዲታወቅ መደረግ አለበት።

ተመልካቾች ድምጽ መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ ሆነውስበሰባዎቹን መካፈል የሚችሉ ሲሆን በአከባቢ የትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ስምምነት በስብሰባ ላይ እንዲገኙ ሊፈቀድላቸው ይችላል። የስብሰባ ማስታወቂያዎች በተቻለ ፍጥነት ለትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ መቅረብ አለበት።

ስብሰባ ዝግ ሊሆን የሚችልበት ብቸኛው ጊዜ ሚስጥራዊ የሆኑ መረጃዎች ላይ ውይይት በሚደረግበት ጊዜ ብቻ ይሆናል (ገጽ 13ን ይመልከቱ)።

**ጥያቄ 9፡ የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን የስበሰባ ቃለ ጉባኤዎች ሚስጥራዊ ናቸው?**

**ጥያቄ 9፡** የሰበሰባዊቹ ጉባኤዎች ሚስጥራዊ አይደለሙ ስለሆነ የሰብሰባ ማጠቃለያ መሆን አለባቸው፤ የቃል በቃል የተጻፉ መሆን የለባቸውም። ሚስጥራዊ የሆኑ ነገሮች ሕዝባዊ በሆኑ ቃለ ጉባኤዎች ውስጥ መጠቃለል የለባቸውም (ገጽ 14ን ይመልከቱ)። ማስታወቂያዎቹ ዝግ የሆኑ/ሚስጥራዊ የሆኑ ክፍለ ጊዜን ማመላከት አለባቸው።

ቃለ ጉባአዎቹ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ወላጆች እና ሠራተኞች ሊያነቧቸው በሚችሉት ቦታ ላይ መለጠፍ ያለባቸው ሲሆን በታቻለ ፍጥነት ስብሰባው ከተደረገ ቢበዛ 20 ቀናት ሳይሆነው ወደ ቤተሰብ እና ሕዝብ አሳታፊ ቢሮ መላክ አለበት። (ገጽ 14ን ይመልከቱ)። ቃለ ጉባኤዎቹ በኢንቴርኔት ቀጥታ መስመር ላይ መለጠፍ እንዲችሉ በofpe.info@dc.gov ላይ በኢሜል መላክ አለባቸው።

---

**ጥያቄ 10፡ የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን የትምህርት ቤቱን ሠራተኞች ጉዳይ ሊመለከት ይችላል?**

**ጥያቄ 10፡** አይችልም። የሠራተኞች ጉዳይ በትምህርት ቤቱ አመራሪ እና ጉዳቱ በደረሰበት ሠራተኞች መፍትሔ የሚሰጥባቸው ሲሆን ጉዳዮቹም ከአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ሥልጣን በላይ ነው።

---

**ጥያቄ 11፡ የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን አባል ስብሰባ መካፈል ካልቻለ፣ በእርሱ ፈንታ ሌላ ሰው እርሱን ተክቶ ስብሰባው ላይ መቀመጥ ይችላል?**

**ጥያቄ 11፡** አይችልም። በዚያ ፈንታ የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን አባል ከስብሰባው ቀን ተከትሎ የስብሰባውን ቃለ ጉባኤ ቅጂውን ለመውሰድ ነገሮች ማመቻቸት አለበት (ገጽ 8ን) ይመልከቱ።

---

**ጥያቄ 12፡ ለአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን የስብሰባ አጀንዳዎችን የሚቀርጸው ማን ነው?**

**ጥያቄ 12፡** አጀንዳው ከአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ሊቀመንበር፣ ከአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን አባላት እና ከርዕሰ መምህሩ ጋር በመመካከር ይቀረጻል። አጀንዳውን ቢያን ከስብሰባው ቀን ከአንድ ሳምንት በፊት ቀደም ብሎ ለአባላት እና ለርዕሰ መምህር በሙሉ መላክ አለበት (ገጽ 13ን ይመልከቱ)። በጊዜው፣ አጀንዳው መፍትሔ ለመስጠት አስቸኳይ እርምጃን የሚፈልግ ጉዳይ ላይ በቃለ ጉባኤው መጨረሻ ላይ ማካተት ይቻላል።

---

**ጥያቄ 13፡ ጥያቄዎች ቢኖሩ የአከባቢ ትምህርት ቤት አማካሪ ቡድን ተጠሪ ማን መሆን አለበት?**

**ጥያቄ 13፡** በ ofpe.info@dc.gov ኢሜል ያድርጉ ወይም በ 202.719.6613 ላይ ይደውሉ እና በ24 ሰዓት ውስጥ የቤተሰብ እና ከሕዝብ ግንኙነት ቢሮ የሠራተኞች አባል መልስ ይሰጥዎታል።